

Empowered lives.
Resilient nations.

# የኢትዮጵያ
# የ2018 የሰብዓዊ ልማት ሪፖርት

- የኢትዮጵያ የ2018 የሰብዓዊ ልማት ሪፖርት ኣካታች የኢንዱስትሪ ልማትና ዘላቂ የሰብዓዊ ልማት ለወጣቶች የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ እንዲሁም መደበኛነትን ያልተከተለ የአሰራር ችግርን በመፍታት እና ከከተሞች መስፋፋት ጋር ያለውን ውስብስብ ቁርኝትን የሚዳስስ ሲሆን የመዋቅራዊ ለውጥ ኣዝጋሚነትን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን በማሳደግ ኢንቨስትመንትን ማሳደግ ይቻላል። የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን የሰብዓዊ ልማትን ማሳደግ የሚችለው ሀብትን መፍጠር የሚችል ዘመናዊና የሰለጠነ ኢኮኖሚና በተጓዳኝነትም የሰው ሃይል ብቃትን በማጐልበትና ሰብዓዊ ነፃነቶችን በማስፋት የግልና የወል ፍላጐቶችን ማሟላት የሚችል ሆኖ ሲገኝ ነው።

- የ2018 ብሔራዊ የሰብዓዊ ልማት ሪፖርት የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ልማት ሂደት አካታች ወይንም ሁሉን አቅፍ ዕድገትን እንዲያስገኙ ሆነው መመራት እንዳለባቸው ያሳያል። ይህ ማለት የሰብዓዊ ልማትን የሚደግፉ፣ መሰረታዊ የሰብዓዊ መብቶችን ለሁሉም የሚያከብሩ፣ እንዲሁም ልዩነቶችን የሚያጠቡ ስልቶችና የኢትዮጵያውያን ምርጫዎችን የማስፋት ግብ ያላቸው እንዲሆኑ ማድረግ ማለት ነው።

- ማዕቀፉ ፖሊሲ፣ የመንግስት የልማት ስራዎች በኢንዱስትሪ ልማትና በሰብዓዊ ልማት መካከል አውንታዊ የግብረ-መልስ ትስስር በመፍጠርና አሉታዊ ውጤቶችን በመቀነስ ረገድ ያላቸውን ጠቃሚ ሚና ያሳያል። እነዚህ ጠቃሚ ሚናዎች የግሉን ዘርፍ ልማት በማጐልበት የሚደገፉ ናቸው። ይህም ለአንስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በሚደረግ ድጋፍ የተሻለ የኃይል፣ የመንገዶች፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎቶችን ጨምሮ የመሰረተ-ልማት ግንባታን የሚያካትትና የኢንዱስትሪ መሠረት የሆነውን ግብርናን በማሳደግ ይሆናል። አግባብነት ያላቸው ፖሊሲዎች፣ የመዋዕለ-ነዋይ ወጪዎችና የመንግስት ተሳትፎዎች፤ አካታች ወይንም ሁሉን-አቅፍ የኢንዱስትሪ ልማትን የሚያጠናክሩ የሰብዓዊ-ልማት ውጤቶች ለማጐልበት፡ አስፈላጊ ሁኔታዎች ናቸው። ይህም የሚረጋገጠው በተሻለ የትምህርትና የጤና-አጠባበቅ ለኢንዱስትሪ ሥራ መሠረት የሆነውን የኑሮ ደረጃ በማሻሻል ይሆናል።
- በኢንዱስትሪ የልማት ሂደት ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎና አመራር ማረጋገጥ ወሳኝ ጉዳይ ነው። ከዚህ አኳያ የእኩል ተጠቃሚነትን በተመለከተ ብቻ ሳይሆን፤ ለስርዓተ-ፆታ እኩልነት ዕንቅፋት የሆኑትን መሰናክሎች ማስወገድና ለኢንዱስትሪ ልማቱ አስተዋፅኦ የማድረግ አቅም ስለሚኖረው ሴቶችን ማብቃት በተለያዩ እርከኖች አፅንዖት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል።

- የኢንዱስትሪ ልማት በከፍተኛ የሰብዓዊ ልማት ደረጃ ላይ ከደረሱት ሃገሮች ጋር በዋናነት የሚያያዝ ቢሆንም፤ በኢንዱስትሪ ልማትና በሰብዓዊ ልማት መካከል ቀጥተኛ ግኑኝነት የለም።

- በሀገራችን ያለው የሰብዓዊ ልማት እውነታ በኢትዮጵያ ውስጥ በክልል ደረጃ ካለው ሁኔታ ጋር ተከፋፍሎ ሲታይ ውጤቱ ተመሳሳይ ነው። ካለው የኢንዱስትሪ ልማት ደረጃ በክልል ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ቁጥር ጋር ሲነፃፀር፡ በኢትዮጵያ ክልላዊ የሰብዓዊ ልማት አመላካች (HDI) የሚያመለክተው ቀጥተኛ ያልሆነ ውስብስብና ቅጽበታዊ ያልሆነ ግኑኝነት መሆኑንም ጭምር ነው። ስለሆነም ሪፖርቱ የኢንዱስትሪ ልማት ሂደት የሰብዓዊ ልማትን ቀዳሚ ግብ በማድረግ መከናወን ያለበት መሆኑን ያስገነዝባል።

- ሪፖርቱ በሰብዓዊ ልማትና በኢንዱስትሪ ልማት መካከል ተመጋጋቢ (Two-Way) ግኑኝነት መኖሩን የሚያረጋግጥ ሲሆን ሀገራዊውና ክልላዊ እውነታዎችን ይመለከታል። በዚህ ሪፖርት የሀረሪ ክልል እ.ኤ.አ. ከ2012/13 ጋር ሲነፃፀር ከዝቅተኛ የዕድገት ወለል ላይ የተነሳ ቢሆንም ከፍተኛውን ዕድገት አስመዝግቧል። እንደ ሪፖርቱ ግኝት ሁሉም ክልሎች ዕድገት ሲያሳዩ የአዲስ አበባ መስተዳደር ከነበረበት የአንደኝነት ደረጃ ወደ አምስተኛ ደረጃ በመንሸራተት ዝቅተኛውን ዕድገት አስመዝግቧል።

**ምስል 1.1**

**የጽንሰ-ሐሳብ ማዕቀፍ: የሰብዓዊ ልማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር**




- በዝቅተኛ የሰብዓዊ ልማት ምድብ ውስጥ ያሉት 40 ሃገሮች በሰብዓዊ-ልማት አመልካች መሠረት ከ0.500 ነጥብ በታች ያስመዘገቡ ሃገሮች ናቸው። ከእነዚ ሀገሮች መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ብትሆንም ካለፉትን 15 ዓመታት ወዲህ ግን ጠንካራ ዕድገት ማስመዝገብና ዕድገቱንም ማስቀጠል ችላለች።

- በስርዓተ-ፆታ ልዩነት እና በኢንዱስትሪ ልማት መካከል ያለው ግኑኝነት በአጠቃላይ ጠንካራና አዎንታዊ ነው። ይህም ማለት የኢንዱስትሪ ልማት ለላቀ የስርዓተ-ፆታ እኩልነት መንገዶችን ከፋች ነው። ቢሆንም ግን ግኑኝነቱ ቀጥታም አስፈላጊም አይደለም። ማዕቀፉና ያለው ማስረጃ በአፅንዖት የሚገልፁት የኢንዱስትሪ ልማት ሂደቱ የሴቶችና ከሴት ልጆች በተጨማሪ ለርትዕ ዕንቅፋት የሆኑትን መሰናክሎች በማስወገድ መላው ሕብረተሰብንም ጭምር ተጠቃሚ የሚያደርግ በሰብዓዊ ልማት ውስጥ ለስርዓተ-ፆታ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጪ የሆኑ ውጤቶችን በሚያረጋግጥ አግባብ መመራት እንዳለበት ነው።

- የኢንዱስትሪ ልማት በሰብዓዊ ልማቱ ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ረገድ የሥራ ዕድል ፈጠራ ዋናው ቀጥተኛ መንገድ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፤ የኢንዱስትሪ ልማት ምቹና አካታች የሆኑ በቂና አዳዲስ የስራ ዕድሎችን የመፍጠር አቅም ያለው ካልሆነ በስተቀር አዎንታዊ ተጽዕኖው ቅጽበታዊ አይደለም። ከ15-64 የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝና ሥራ ላይ መሰማራት የሚችል ከፍተኛ የሠራተኛ ክፍል ባለበት ሁኔታ የዕድሜ ስብጥሩ በሰጠው ዕድል መጠቀም የመቻል ጉዳይ የሚመሠረተው ባለው የፖሊሲ ምህዳር ላይ ይሆናል። ስለሆነም የዕድሜ ስብጥሩ ሽግግርን ለማፋጠንና ከስብጥሩ በሚገኝ ዕድል ለመጠቀም እንዲቻል  የታሰበበትና የተቀናጀ የፖሊሲ ማዕቀፍ አስፈላጊ ይሆናል።

- በሀገሪቱ የኢንዱስትሪ ልማት ዐውድ ውስጥ የሥራ ገበያው የክህሎት ማበልጸጊያ እና የቅጥር ሁኔታ ያለበትን ሁኔታ በማጥናት ሪፖርቱ ወጣቶችና ሴቶች ከሥራ ገበያው በሚፈለገው መጠን ተጠቃሚ አለመሆናቸውን ያረጋግጣል። ለሴቶች ከተገቢው በታች በሚሰጥ ዝቅተኛ ክፍያ የሚገለፅ የፆታ የደምወዝ ልዩነት እና አምራች ዘርፍን ጨምሮ በሁሉም ዘርፎች ሴቶችን በዝቅተኛ ደረጃ ሥራዎች ላይ በመመደብ የሚፈፀመው መድልዎ የሚያመለክተው የኢንዱስትሪ ልማቱ ለኢትዮጵያ የሰብዓዊ ልማት ዕድገት አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ቅድሚያ ተስጥቶአቸው ሊሰሩ የሚገቡ መሆናቸውን ያመላክታል።

- ሪፖርቱ በኢንዱስትሪ ልማት ላይ ከሚደረግ ከፍተኛ ትኩረት ሊመነጭ ከሚችልና በሕይወት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጐጂ ችግሮች የሚገኙበትን ሁኔታ ይዳስሳል። ከችግሮቹ በዋናነት ሠራተኛው ወደ ኢንዱስትሪ ዘርፍ በሚዞርበት ግዜ የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማረጋገጥ፣ በአካባቢና በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚከሰተውን ጐጂ ተፅዕኖ ለመቀነስ፤ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ልማት ግቦችን ለማሳካት በሚደረግ ጥረት ለዜሮ-የካርቦን ልቀት ያለውን ቁርጠኝት ለማስቀጠል እና መደበኛ ያልሆነና ያልተገደበ የከተሞች መስፋፋት የሚያስከትሉት ችግሮች ናቸው።

- የኢትዮጵያው ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ የኢኮኖሚ ዕድገት (CRGE) ሀገሪቱ ወደ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች አልፎ በመሻገርና በታዳሽ ኤነርጂ ለሚጠቀሙ ኢኮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማትና ለኤነርጂ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎች ቅድሚያ በመስጠት የአረንጓዴ ኢንዱስትሪ ዘርፍን ለመገንባት መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል። ያም ሆኖ በሥራ ቦታ ላይ የቆሻሻ አያያዝን በተመለከተ በየአካባቢው ቆሻሻን የመልቀቅ/የማራገፍ ተግዳሮትን ለመፍታት፤ ሃገሪቱ ስኬታማና የተቀናጀ የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት ያስፈልጋታል።

| ዘርፎች | ለጥቅል ሃገራዊ ምርት ያለው አስተዋፅኦ በ% | ዓበይት ከባቢያዊ ተግዳሮቶች | መራቆት ያስከፈለው ዋጋ |
|---|---|---|---|
| ኢንዱስትሪና ማኑፋክቸሪንግ | በ2012 13% እና 4%<br>በ2025 27% እና 17% | የውሀ፣ የአፈር፣ የአየር ብክለት | ጥቅል የጐጂ ጋዝ ልቀት ዕድገት ትንበያ በተለመ ደው አሰራር:_ በዓመት 16% ሆኖ በ2030 71 ሜትሪክ ቶን Co2e<br>ከዉሀ በካዮች የሚኖሮው ልቀት:_ካሉት ኢንዱስትሪዎች ላይ ከ18,543 ኪ.ግ./በቀን፡ ወደ 32,182 ኪ.ግ./በቀን ከፍ ብሏል |

ምንጭ፡ የዓለም ባንክ የ2017 የኢትዮጵያ የአረንጓዴ ትራንስፎርሜሽን ሃገራዊ ጥናት።

## የሪፖርቱ ዋና ዋና ግኝቶች

- የኢትዮጵያ የሰብዓዊ ልማት ከትምህርትና ከገቢ ንዑስ አመላካቾች ጋር ሲነፃጸር እጅግ ከፍተኛውን አስተዋፅኦ የሚያበረክተው አማካኝ የሰው ዕድሜ ሲሆን ለዚህ መነሻው የጤና ዘርፍ ውጤቶች ናቸው ማለት ይቻላል። በጤና ንዑስ አመላካች ደረጃ ላይ ስትቀመጥ ኢትዮጵያ ዝቅተኛ የሰብዓዊን ልማት አመላካች ደረጃ ካላቸው ሰባት የዓለም ሃገሮች መካከል አንዷ ስትሆን በትምህርት አመላካችም የኢትዮጵያን የሰብዓዊ ልማት ዝቅተኛ ያደረገው በንፅፅር የትምህርት ዕድል ያለማግኘት በምክንያትነት ይጠቀሳል።

- እ.ኤ.አ. ከ2012/13 ጀምሮ የሰብዓዊ ልማት አመላካች በሁሉም ክልሎች ዕድገት ያሳየ ሲሆን በሁሉም ዞኖች/ወረዳዎች የጤና ንዑስ አመላካች ለሰብዓዊ ልማት ደረጃ ዕድገት አመልካች ዋንኛው ምንጭ እንደሆነ ያሳያል። ሆኖም ግን ሀረሪ ክልል በጤናው ንዑስ አመላካች ላይ ወደ ኋላ የተንሸራተተ ብቸኛ ክልል ሲሆን በትምህርትና በገቢ ንዑስ አመላካች ግን በንጽጽር የተሻለ ዕድገትን አስመዝግቧል።

- የትምህርት ስኬት መሻሻል ቢያሳይም በፆታ እንዲሁም በገጠርና በከተማ መካከል ያለው ምጣኔ አሁንም ዝቅተኛ ነው። እ.ኤ.አ. በ2013 ዕድሚያቸው 10 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑት 32% ወንዶች እና 51% ሴቶች የትምህርት እድል አልነበረም። ከዚሁ ጋር ዕድሜያቸው በትምህርት ላይ መሆን ከሚገባቸው ውስጥ 1.8% የሚሆኑት ብቻ ቢያንስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን አጠናቀዋል። የትምህርት ወጪ በተነፃፃሪነት ከፍተኛ ቢሆንም፡ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ውጤታማነቱ አሁንም ዝቅተኛ እንደሆነ በተለይም በትምህርት ጥራት ላይ ጫና አሳርፈዋል።

- በኢትዮጵያ በጋብቻ ውስጥ ካሉት ሴቶች የዘመናዊ የወሊድ መቆጣጠሪያ አጠቃቀም ባለፉት 16 ዓመታት እ.ኤ.እ. በ2000 ከነበረበት 6 በመቶ፡ በ2016 ወደ 35 በመቶ አድጓል። ይህ አሀዝ ከፍተኛ ገቢ ያላቸውን ሃገሮች ሳይጨምር 24 በመቶ ላይ ከሚገኘው የሰሓራ በታች አህጉራዊ አማካኝ ጋር ሲታይ በመጠኑ ከፍ ያለ ነው። ይህም ለወሊድ ምጣኔ መቀነስ አስተዋጽኦ ቢኖሮውም በክልሎች መካከል ግን አሁንም ያልተመጣጠነ የአጠቃቀም ክፍተት ይታያል። ለማሳያነት በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል በጋብቻ ውስጥ ካሉት ሴቶች (ከ15-49 ዕድሜ) እጅግ ዝቅተኛ የሆነ (1%) ዘመናዊ የወሊድ መቆጣጠሪያ አጠቃቀም ሲኖር ኣፋር (በ12%) ይከተላል።

**ምስል 2.7**

**የሰብዓዊ ልማት ንዑስ አመላካቾች በክልል (እ.ኤ.አ 2012/13 እና 2016/17)**



- ሴቶች ያለመቀጠር ዕድላቸው ከወንዶች በሶስት ዕጥፍ ያህል ሊበልጥ እንደሚችል ይታመናል። የሴቶች የነፍስ-ወከፍ ጥቅል ሃገራዊ ገቢ ከወንዶቹ 1,886 ዶላር ጋር ሲነፃፀር 1,161 ዶላር ላይ ይገኛል። ይህ ሁኔታ ሴቶች መሠረታዊ የሰራተኛ መብቶቻቸውን ሊያስከብሩላቸው በማይችሉና ለተለያዩ አደጋዎች ተጋላጭ ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ ያስገድዳቸዋል። ለስርዓተ-ፆታ እኩልነትና ሴቶችን ለማብቃት ሥራ እንቅፋት የሆኑና ለዘመናት የቆዩ ጎጂ ባህላዊ ልማዶች መሰናክሎች ናቸው። ከእነዚህም መካከል በሴቶችና ሴት ልጆች ላይ የሚፈፀም የሀይል ጥቃት እንዲሁም የሴት ልጆች ግርዛትና ያልተመጣጠነ የቤት ውስጥ የስራ ጫና ይጠቀሳሉ።

- አጠቃላይ የደመወዝ ጭማሪ ሳይደረግ ባለበት ቆሟል፡ ወይም ከገንዘብ የመግዛት አቅም አንፃር እንዳሽቆለቆለ ይገኛል። በኢንዱስትሪና በማኑፋክቸሪንግም አማካኝ ደመወዝ ዝቅተኛ ሲሆን ከሃገራዊው አማካኝ ጋር ሲነፃፀር የሴቶቹ ደግሞ ይበልጥ ያነሰ ነው። ይህ ሁኔታ የሥራ ዕድል ፈጠራ የኑሮ ደረጃን በማሻሻልና ድህነትን በመቀነስ ረገድ ትርጉም እንዲኖረው ለማድረግ የሚኖረውን አቅም ይገድበዋል።

- በኢትዮጵያ ሥራ አጥነት ከሞላ ጐደል የከተሞች እውነታ እንደመሆኑ የከተማው ሠራተኛ የሰው ኃይል ውጤታማነትን ማሳደግ ለመዋቅራዊው ለውጥ/ትራንስፎርሜሽን ቁልፍ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የሚያስገኘውን ጥቅም ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች መዳረሳቸውን የሚያረጋግጥ መሆኑም ጭምር ነው። በከተሞች አከባቢ አሁን ያሉት የማህበራዊ ዋስትና አሰራሮች፡ የወጣቶችና የሕፃናት ፍላጐቶችን ለሟሟላት በቂ አይደሉም።

## ቁልፍ የፖሊሲ ምክረ-ሃሳቦች

ለአካታችና ለዘላቂ ሰብዓዊ ልማት እንደ አንድ ማሳኪያ መሳሪያ የተፋጠነና ተወዳዳሪ የሆነ የኢንዱስትሪ/ማኑፋክቸሪንግ ዕድገትን ለማምጣት ሪፖርቱ ተጨባጭ የፖሊሲ ምክረ-ሃሳቦችን ያቀርባል።

### የቀረቡት የፖሊሲ እርምጃ ሃሳቦች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ተመጣጣኝ ክፍያዎችን የሚያስገኙ አስተማማኝ ደህንነታቸው የተጠበቀና ዝቅተኛ የአካባቢ የጤና አደጋ ተጋላጭነት ያላቸው ምቹ የሥራ ዕድሎችንና አካባቢዎችን ማስፋፋት። ከዚህ በተጓዳኝ ለኢንዱስትሪ ልማት ፍላጐት የሚያሟላ የቴክኒክና የሙያ ስልጠናን ጨምሮ በሁሉም ደረጃዎች ጥራት ያለው ትምህርትን በማረጋገጥ፣ የወጣቶች የክህሎት ማበልፀጊያ ሥራን ማፋጠን፤ በዝቅተኛ ገቢ ላይ ለሚገኙት ከሚደረግ ሴፍቲ-ኔት/ማህበራዊ ጥበቃ/ በተጓዳኝ ውጤታማ የኢንፎርሜሽን ሥርዓትና የሥራ ዕድል ፈጠራን ከሥራ ገበያ ጋር መፍጠር አስፈላጊ ነው።

- በትምህርትና በጤና ያለውን የፆታ ልዩነትና ክፍተቶችን በማጥበብ ከኢንዱስትሪ ልማት ለሚገኙ የሴቶች ዕኩል ተጠቃሚነትና ተሳትፎ ዕንቅፋት የሆኑ መሰናክሎችን የማስወገድ፣ ፆታ ነክ ሕጐችንና ደንቦችን በጥብቅ ተፈፃሚ ማድረግ፣ ለሴቶች መብቶች በሚሰሩ የሴቶች ማህበራትን ማጠናከር እና ሴቶችን ከኢንዱስትሪ ሥራዎችና ገቢ ከሚያስገኙ የሥራ ፈጠራዎች የሚገድቡትን ማህበራዊ/ቤተ-ሰብ-ነክ ተግዳሮቶችን መፍታትና ጥረቱንም በቀጣይነት መደገፍ ያስፈልጋል።

- በኢንዱስትሪ ፓርኮች አዳዲስ አሰራሮችና ቴክኖሎጂዎችን መደገፍና ማበረታታት፤ አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል አዳዲስ አሠራሮችንና ቤተ-ሙከራዎችን ማቋቋምን ጨምሮ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ግዴታዎችን ለመተግበርና ለመከታተል በመረጃ በመጠቀም እና ሠው ሰራሽ ኢንተሊጀንስን በመጠቀም የኢንዱስትሪውን የሰው ኃይል ለመጪው ዘመን ሥራዎች ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

- ኢንዱስትሪን በማጣመር አዳዲስ አሠራሮችን እንዲሁም ውድድርንና የዕሴት ሰንሰለት ሥርዓት ተደጋጋፊነትን ለማረጋገጥ በተለያዩ ቦታዎች የኢንዱስትሪ ዕሴት ሰንሰለትን ማበረታታት ያስፈልጋል።

- ሰብዓዊ ልማትን የሚያሳድግና አካታች የሆነ የኢንዱስትሪ ልማትን የሚያበለፅጉ የግብርና፣ የአካባቢ ልማትና የከተማ ልማድ ዕቅዶች ዙርያ የተቀናጀ አሠራርን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

- በመጨረሻም ተወዳዳሪ የሆነ የኢንዱስትሪ እድገት መሠረተ ልማትን፣ የገንዘብ ተቋማት ተደራሽነትንና ተቋማዊ አሰራሮችን ከማጠናከር ጋር እንደ አንድ የኢንዱስትሪ ሽግግር ወሳኝ መነሻ የሆነዉን ዘርፍ ልማት በቀጣይነት ማበረታታትና ማጠናከር ያስፈልጋል።